

# ዘኬዎስ

- ዘኬዎስ ግብር ሰብሰቢ ነበር። በእርግጥም ዘኬዎስ የግብር ሰብሰቢዎች አለቃና ባለጠጋ ሰው ነበር። ግብር ሰብሳቢዎች በሕዝብ እጅግ በጣም የተጠሉ ሰዎች ነበሩ። ምክንያቱም አንዳንድ ጊዜ ከሕዝብ መሰብሰብ ከሚገባቸው በላይ ብዙ ግብር እየሰበሰቡ ለራሳቸው ያስቀሩ ነበርና ነው። ከሰበሰቡት ገንዘብ ለመንግስት የሚያስገቡት የተወሰነውን ብቻ ነበር።

- ግብር የሚሰበስቡ ሰዎች ወደዮሐንስ መጥተው ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ሲጠይቁት ግብር መሰብሰብ ከሚገባቸው በላይ እንዳይሰበስቡ ነገራቸው።

- ግብር ሰብሳቢዎች በመፅሐፍ ቅዱስ ከኃጢአተኞች፣ እምነት ከሌላቸውና ሞራለ ቢስ ከሆኑ ሰዎች ጋር እንደሚቆጠሩ ይናገራል። ሆኖም ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙዎቹ ንስሐ ሊገቡና እውነቱን ተምረው ሊገነዘቡ እንደሚችሉ አሳይቷል። ስለግብር ሰብሳቢውና ስለፈሪሳዊው ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረው ምሳሌ በሁለቱ መካከል ስለነበረው የአመለካከት ልዩነት እያነፃፀረ በግልፅ ያሳያል። ፈሪሳዊው በመልካምነቱና በፅድቁ የሚኮራ

ነበር። ግብር ሰብሳቢው ግን ራሱን አዋርዶ ንስሐ ገባ። ይህንንም ምሳሌ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 18፡ 10-14 ድረስ ባለው ክፍል ውስጥ ማንበብ ትችላላችሁ።

- ዘኬዎስም ልክ እንደዚህ በምሳሌው ውስጥ እንዳየነው ግብር ሰብሳቢ ነው። ኢየሱስን ማየት ፈለገ። ሆኖም ረዥም ሰው አልነበረም። በእድሜ ዘመኑ ብዙ ሰው በተሰበሰበበት አካባቢ ከሆነ ከሰዎች ትከሻና ራስ በላይ አሻግሮ ነገሮችን የመመልከት ችግር ነበረበት። ስለዚህ ኢየሱስ በሚመጣበት ጊዜ ማየት እንዲችል አንድ ኢየሱስ በሚያልፍበት መንገድ ላይ በሚገኝ ዛፍ ላይ ለመውጣት አሰበ።

- ከዚያም አጫጭር እግሮቹ ወደዛፉ አደረሱት። ወደዛፉ ላይም ወጣ። እንዴት ደስ ይላል። ከማንም ይልቅ ኢየሱስን ለማየት አመቺ ቦታ አገኘ።

- ኢየሱስ ዛፉ አጠገብ ሲደርስ ወደዘኬዎስ ቀና ብሎ ተመለከተና ከዛፍ ላይ እንዲወርድ አዘዘው። ወደዘኬዎስ ቤት ለመሄድ ፈለገ። ዘኬዎስ እጅግ በጣም ተደነቀ። ከዛፍ ላይ ወረደ ኢየሱስንም ማስተናገድ ጀመረ።

- ይህን ያዩ ሰዎችም ኢየሱስን ወደኃጢአተኞች ቤት ይሄዳል በማለት ይነቅፉት ጀመር። ሆኖም እነርሱ እንዳሰቡት ሳይሆን ዘኬዎስ ንስሐ ለመግባትና ራሱን ለማዋረድ የተዘጋጀ ልብ ነበረው። እንደውም ከዚህ በፊት ሲያደርጋቸው በነበሩ ኃጢአቶች ተፀፀተ። ካለው ሀብቱም ግማሹን ለድሆች ለመስጠት ቃል ገባ። ያታለለው ሰው ካለም አራት እጥፍ አድርጎ ለመካስ ቃል ገባ። ኢየሱስም በዚህ አጭር ሰው የልብ መለወጥ እጅግ ደስ ተሰኘ። እንዲህም አለ፣ “ዛሬ ለዚህ ቤት መዳን ሆኖለታል።”

የዘኬዎስን ታሪክ በሉቃስ ወንጌል በምዕራፍ 19፡1-10 ባለው ክፍል ውስጥ ማንበብ ትችላላችሁ።

http://gardenofpraise.com